# ሄፓቲቲስ (የጉበት በሽታ) A ክትባት

## ማወቅ የሚገባዎት

Many Vaccine information Statements are available in Spanish and other languages. See www.immunize.org/vis

Hojas de información sobre vacunas están disponibles en español y en muchos otros idiomas. Visite www.immunize.org/vis

## 1 መከተብ ለምን አስፈለገ?

የጉበት በሽታ A ከባድ የጉበት ህመም ነው። የሚከሰተው በጉበት በሽታ A ቫይረስ (HAV) ነው። HAV ከሰው ወደ ሰው የሚተላለፈው በበሽታው ከተጠቁ ሰዎች አይነምድር ጋር በሚኖር ንክኪ ሲሆን፣አንድ ሰው እጁን ወይም እጇን በትክክል ካልታጠቡ በቀላሉ የሚከሰት ነገር ነው። በ HAV በተበከለ ምግብ፣ ውሃ፣ ወይም ዕቃዎች የጉበት በሽታ A ሊይዝዎት ይችላል።

የጉበት በሽታ A ምልክቶች እነዚህን ሊያጠቃልሉ ይችላሉ፡-

- ትኩሳት፣ድካም፣የምግብ ፍላጎት ማጣት፣ማቅለሽለሽ፣ማስታወክ፣ እና/ወይም የመገጣጠሚያ ህመም
- ከባድ የሆድ ህመም እና ተቅማጥ(በዋነኝነት በህፃናት)፣ ወይም
- ወይበ (ቢጫ ቆዳ ወይም ዓይኖች፣ ጠቆር ያለ ሽንት፣ ሸክላ-ቀለም ያለው የአንጀት እንቅስቃሴዎች)።

ከተጋለጡ ከ 2 እስከ 6 ሳምንታት ውስጥ እነዚህ ምልክቶች የሚታዩ ሲሆኑ እስከ 2 ወር ይቆያሉ፣ ቢሆንም አንዳንድ ሰዎች እስከ 6 ወር ሊታመሙ ይችላሉ። የጉበት በሽታ A ካለብዎት ስራ መስራት እስከማይችሉ ድረስ በጣም ሊያምዎት ይችላል።

ልጆች ብዙ ጊዜ ምልክቶቹ አይታይባቸውም፣ አዋቂዎች ላይ ግን ይታያል። ምልክቱ ሳይታይብዎት HAVን ማሰራጨት ይችላሉ።

የጉበት በሽታ A የጉበት ከጥቅም ውጪ መሆንን እና ሞትን ሊያስከትል ይችላል፣ ቢሆንም ይህ ያልተለመደ ሲሆን የሚከሰተውም የ 50 አመት እድሜ እና ከዚያ በላይ በሆኑ ሰዎች እና በሌላ የጉበት በሽታ፣ ማለትም በጉበት በሽታ B ወይም C የተጠቁ ሰዎች ላይ ነው።

**የጉበት በሽታ A ክትባት የጉበት በሽታ A ን መከላከል ይችላል።**የጉበት በሽታ A ክትባቶች የተሰጡት በዩናይትድ ሰቴትስ ከ 1996 ጀምሮ ነው። ከዚያ ጊዜ ጀምሮ፣ በ ዩ.ኤስ. በየአመቱ የሚገለፀው የማህደር ቁጥር ከ 31,000 ማህደሮች ወደ 1,500 ማህደሮች ቀንሷል።

## 2 የጉበት በሽታ A ክትባት

የጉበት በሽታ A ክትባት ደካማ (የሞተ) መድሃኒት ነው፡ ፡ ለዘላቂ ጥበቃ**2 ጊዜ** መከተብ ያስፈልግዎታል። እነዚህ ክትባቶች በትንሹ በ 6 ወራት ያህል መራራቅ አለባቸው።

ልጆች በተደጋጋሚ የሚከተቡት በመጀመርያ እና በሁለተኛው ልደታቸው (12 እስከ 23 ወራቶች) መሃል ነው። ትላልቅ ልጆች እና ታዳጊዎች ክትባቱን ከ 23 ወራት በኋላ ማግኘት ይችላሉ፡ ፡ ከዚህ በፊት ያልተከተቡ አዋቂዎች እና ከጉበት በሽታ A መጠበቅ የሚፈልጉ ክትባቱን ማግኘት ይችላሉ።

የጉበት በሽታ A ክትባትን በእነዚህ ምክንያቶች ማግኘት አለብዎት፡

- የጉበት በሽታ A ቋሚ ወደ ሆኑባቸው ሃገሮች የሚጓዙ ከሆነ፣
- ወንድ ሆነው ከሌላ ወንድ ጋር ግብረ ስጋ ግንኙነትን ከፈፀሙ፣
- ህገ ወጥ መድሃኒቶችን ከተጠቀሙ፣
- ለረጅም ጊዜ የቆየ የጉበት በሽታ እንደ የጉበት በሽታ B የጉበት በሽታ C ካለብዎ፣
- በደም መርጋት ክምችት ክትትል ሲደረግልዎ ከነበረ፣
- በጉበት በሽታ A በተጠቃ እንስሳ ላይ ሲሰሩ ከነበረ ወይም በጉበት በሽታ A የምርምር ቤተ ሙከራ ውስጥ፣ ወይም
- የጉበት በሽታ A ቋሚ ከሆነበት ሃገር የመጣ አለም አቀፋዊ ማደጎ ከሆነ ሰው ጋር የግል ቅርብ የሆነ ንክኪ እንደሚኖርዎ የሚጠብቁ ከሆነ

ስለ እነዚህ ቡድኖች ተጨማሪ መረጃ ከፈለጉ የጤና ጥበቃ አቅራቢዎን ይጠይቁ።

የጉበት በሽታ A ክትባትን ከሌሎች ክትባቶች ጋር አብሮ መስጠቱ ስለሚያስከትለው ስጋት በተመለከተ የሚታወቅ ነገር የለም።

## 3 አንዳንድ ሰዎች ይህንን ክትባት መውሰድ የለባቸውም

ክትባቱን ለሚሰጠው ሰው መንገር ያለብዎት፡

- **ከባድና ህይወትን አደጋ ላይ ሊጥል የሚችል አለርጂ ካለብዎ።**
  ከዚህ በፊት ከወሰዱት ከ meningococcal ACWY ክትባት የተነሳ ህይወትን አደጋ ላይ የሚጥል አለርጂ ከተነሳብዎ ወይም ከዚህ ክትባት ጋር በተያያዘ ከባድ አለርጂ አጋጥሞዎ የሚያውቅ ከሆነ፣ ይህንን ክትባት አይውሰዱ። ስለ መርፌው አካሎች መረጃ ከፈለጉ የጤና ጥበቃ አቅራቢዎን ይጠይቁ።

- **ደህንነት ካልተሰማዎት።**
  እንደ ብርድ ያለ መጠነኛ ሕመም ካለብዎ፣ ዛሬ መርፌ ማግኘት ይችላሉ። በመጠኑ ወይም በከባድ ሁኔታ ታመው ከሆነ፣ እስከሚድኑበት ጊዜ መጠበቅ ይኖርብዎታል። ሃኪምዎ ሊያማክርዎት ይችላል።



U.S. Department of Health and Human Services
Centers for Disease Control and Prevention

## 4 | የክትባት አፀፋዊ ምላሽ ስጋቶች

በምንም ዓይነት መድሃኒት፣ መርፌን ጨምሮ፣ የጎንዮሽ ችግሮች ሊኖር የሚችልባቸው እድሎች አሉ። እነዚህ ቀላል እና በራሳቸው ጊዜ የሚጠፉ ናቸው፣ነገር ግን ከባድ የሆኑ አፀፋዊ መልሶችም ሊኖሩ ይችላሉ።

የጉበት በሽታ A መርፌን የሚያገኙ ሰዎች ምንም አይነት ችግር ከዚህ ጋር የላቸውም።

**ጥቃቅን ችግሮች** የጉበት በሽታ A መርፌን ተከትሎ ያሉ ጥቃቅን ችግሮች እነዚህን ያጠቃልላሉ:
- መርፌው የተሰጠበት በታ ላይ መቁሰል ወይም መቅላት
- ዝቅተኛ ትኩሳት
- ራስ ምታት
- ድካም

እነዚህ ችግሮች የሚከሰቱ ከሆነ ከ 1 እስከ 2 ቀን ይቆያሉ።

ሃኪምዎ ስለ እነዚህ ምልክቶች ሊነግሩዎት ይችላሉ።

**ክትባቱን ከወሰዱ በኋላ የሚያጋጥሙ ችግሮች:**

- ከህክምና በኋላ፣ ክትባትን ጨምሮ ሰዎች አንዳንድ ጊዜ ራሳቸውን ይስታሉ። ለ15 ደቂቃ መቀመጥ ወይም መተኛት ራስን መሳት፣ እንዲሁም በመውደቅ የሚመጣውን ጉዳት ይከላከላል። የድንዛዜ ስሜት፣ የእይታ ለውጥ ወይም ጆሮ ውስጥ ማቃጨል ከተሰማዎት ለሀኪምዎ ይንገሩ።
- አንዳንድ ሰዎች ትከሻ ላይ ከበድ ያለ ህመም ሲሰማቸው የተወጉበት እጃቸውን ማንቀሳቀስ ያስቸግራቸዋል። ይህ አልፎ አልፎ የሚከሰት ነው።
- የትኛውም መድኃኒት ከበድ ያለ የአለርጂክ አፀፋዊ ምላሽ ሊያስነሳ ይችላል። ከክትባት የሚመጡ አለርጂኮች በጣም አልፎ አልፎ የሚከሰቱ ሲሆኑ ከ አንድ ሚሊዮን ክትባቶች ውስጥ በ 1 እንደሚከሰት ይገመታል፤ የሚከሰተቱትም ክትባቱ ከተሰጠ በኋላ ከጥቂት ደቂቃዎች እስከ ጥቂት ሰዓታት ባለው ጊዜ ውስጥ ነው።

ልክ እንደ ሌላው መድኃኒት፣ ክትባት በጣም ከባድ ጉዳት ወይም ሞት የሚያስከስትበት በጣም ጠባብ እድል አለ።

የክትባቶች ደህንነት ሁሌጊዜ በቅርብ ክትትል ውስጥ ነው። ለበለጠ መረጃ ይህን ይጎብኙ፡ **www.cdc.gov/vaccinesafety/**

## 5 | አደገኛ የሆነ የአለርጂ ምልክት ቢኖርስ?

**ማየት ያለብኝ ምንድነው?**
- ስጋት የሆነብዎትን ነገር እንደ ከባድ የአለርጂክ ምልክት፣ ከፍተኛ ትኩሳት ወይም ያልተለመዱ ባህርያትን ይመልከቱ።

  **የከባድ አለ**ርጂክ ምልክቶች የሚያካትቱት ሽፍታዎች፣ የፊትና የጉሮሮ እብጠት፣ የመተንፈስ ችግር፣ ፈጣን የሆነ የልብ ምት፣ መደንዘዝ እና ድካም ናቸው። ይህም ከክትባት በኋላ ከትንሽ ደቂቃ እስከ ትንሽ ሰዓት ውስጥ ይጀምራል።

**ምን ማድረግ አለብኝ?**
- **ከባድ የሆነ የአለርጂክ ምልክት** ወይም ሊቆይ የማይችል አስቸኳይ ከመሰለዎት 9-1-1 በመደወል አቅራቢያ ወዳለው ሆስፒታል ይሂዱ። ካለበለዚያ ሀኪምዎ ጋር ይደውሉ።

  ከዚያ በኋላ የአለርጂው ምልክት ለ “Vaccine Adverse Event Reporting System” (VAERS) ሪፖርት መደረግ አለበት። ሃኪምዎ ይህንን ፋይል ሪፖርት ማድረግ አለበት ወይም እርስዎ ራስዎ የ VAERS ድረ ገጽን በ **www.vaers.hhs.gov**, በመጠቀም ወይም በ**1-800-822-7967**መደወል ይችላሉ።

VAERS የህክምና ምክር አይሰጥም።

## 6 | The National Vaccine Injury Compensation Program

የ National Vaccine Injury Compensation Program (VICP) የፌደራል ፕሮግራም ሲሆን በክትባት ጉዳት ለደረሰባቸው ሰዎች ካሳ የሚሰጥ ነው።

በክትባት ጉዳት እንደደረሰባቸው የሚያስቡ ሰዎች ስለ ፕሮግራሙ ለማወቅ እና መጠየቂያ ለመሙላት በ **1-800-338-2382, www.hrsa.gov/vaccinecompensation**። የካሳ ጥያቄ ለመጠየቅ የጊዜ ገደብ አለው።

## 7 | እንዴት የበለጠ ማወቅ እችላለሁ?

- የጤና እንክብካቤ ሰጪዎን ይጠይቁ። እርሱ ወይም እርሷ የክትባቱን ማብራሪያ ወረቀት ወይም ሌላ የመረጃ ምንጭን መጠቆም ይችላል/ትችላለች።
- ወደ እርስዎ ግዛት የጤና ዲፓርትመንት ጋር ይደውሉ።
- Centers for Disease Control and Prevention (CDC) ን ያግኙ፡
  - **1-800-232-4636** (**1-800-CDC-INFO**) ይደውሉ ወይም
  - የ CDC ን ድረ ገጽ በ **www.cdc.gov/vaccines**


DCH-0452AM
AUTH: P. H. S., Act 42, Sect. 2126.

Vaccine Information Statement
Hepatitis A Vaccine - Amharic
7/20/2016
42 U.S.C. § 300aa-26

Office Use Only

Translation provided by Minnesota Department of Health

**የሕክምና እንክብካቤ አገልግሎት ሰጪ(ዎች) ትክክለኛ የክትባት ሁኔታ መረጃ እንዲኖራቸው፣ የክትባት ግምገማ፣ እና ለወደፊት ክትባቶች የቀረበ መርኃ ግብር ለመፍቀድ መረጃ ለምችጋን እንክብካቤ ማሻሻያ መዝገብ ቤት** (Michigan Care Improvement Registry) **ይላካል። የሕክምና እንክብካቤ አገልግሎት ሰጪአቸው የክትባት መረጃ ለመዝገብ ቤቱ እንዳያቃብል ለመጠየቅ ግለሰቦች መብት አላቸው።**